# ይቅር በለን ሰይጣን!

## ከኣባ ቤክሲሣ

ስብዕናችን ተናጋ፣
ወሮ-በላ ተባብሮ፣
ኀጠኘነት ነገሰ፣
ዳር ድንበራችን ተሰብሮ።

ሞትነው የዉሻን ሞት፣
ፈጣሪ እንደተሳነው፣
ቀባሪ እንደቸገረው፣
አሥራት እንደበላ ገበዝ፣
እርግማን እንደተጫነው።

ያም ሆኖ!
ሁሉን ቻልነው እንደቁጣ፣
ሊያስተምረን ሃጥያንን ከፈጣሪ እንደመጣ።

ምነው ጌታ!
ላኀደሉት የምትሞላ፣
ለጨከኑት የምትራራ።
ለግፈኞች እድሜ ችረህ፣
ሰቃያችንን አርዝመህ።
በል ተጠየቅ መልስ አለብህ፣
ለኛ መስሎን ሰቅላትህ፣
ግርፋትህ።

ይባስ ብለህ፣
በደካሞች መጨከንህ፣
ኣንተን ያመኑ የወለዱ፣
የፆሙም የሰገዱ፣
ልጆቻቸው በርሳሥ ነደዉ፣
የርሳሥ ዋጋ በደም ከፍለው፣
ማብቂያ በሌለው ፍዳ በእግረ ሙቅ ተቀፍድደው፣
ኣንድየ መባልህንስ ለምን ከግፍ አትቆጥረዉ?

ካልሆነማ!
ትንሳዔህም ከራቀማ፣
ባልዋልክበት ባልፈየድከዉ፣
መለመንህ ለምንድነዉ?
ካልታደግከን እንደትውልደ፣
ጌታ ፍረድ ወይም ዉረድ።

ይልቅ ሰይጣን!
ተክህኖህ ፍርደ-ገምድል፣
የስቅላት ባለሟሉ፣
የሙስና ሊቀጳጳሥ፣
ሓሰት እብሪት በቀል ገድሉ።

የጣር የመከራ ስልጡን፣
ጸረ-ፍቅር ጸረ-አንድርነት
የዉርደት ሊቀካህን፣
የፅርዛት የምንዝራት።

የትዉልድ ዉርሰ እርግማን፣
አንተ የሞት ባለስልጣን፣
ሁለት ዓሥርት አመታትን፣
ያጋደልከን ያፋጀኸን፣
የስዉ ቀደምት እንዳልነበርን ባደባባይ ያዋረድከን፣
ያስለመንከን፣
ያላመድከን፣ “ምንተስሟ ለማርያምን”።

ወይ ነዶ!
ሞትን በሞት እንዳንቀጣዉ
ቂምን በደም በመበቀል፣
ፈጣሪያችንን ፈራነዉ፣
እሱም በተራዉ ይቆጣል።

ኣንተ ምሩቅ! በዘር ማጥፋት ግብርና፣
ቅስማችንን ሰብረህዉ ሞራላችን ነቅዞኣልና።

ከዚህ ወዲያሥ ይለይለት!
ባንተዉ መጀን ክቡር ሰይጣን!
እባክህን ይቅር በለን!
የወለድነዉ ባንተ ኣይዉጣ፣
መለስ ቀለስ ኣታድርገን።

ከኣባ ቤክሲሣ
beksisaa@yahoo.com